
### *የጡት ካንሰር*

የጡት ካንሰር ሴቶችን በከፍተኛ ደረጃ ከሚያጠቁት የካንሰር አይነቶች አንዱ ነው

የጡት ካንሰር የጡት ሴሎች መለወጥና ከቁጥጥር ውጪ በሆነ መንገድ መራባት ወይም መባዛት የሚመጣ የካንሰር ዓይነት ነው

ብዙውን ግዜ የወተት ማንቆርቆሪያ ትቦ (milk duct) ወይም የወተት ማመንጫ ገንዳ (Lobular gland) ሲያጠቃ ይታያል ይህ በሽታ ብዙውን ግዜ ሴቶችን ሲያጠቃ ወንዶችንም አልፎ አልፎ ያጠቃል




ለበሽታው ሊጋለጡ የሚችሉ ቅድመ ሁኔታዎች (risk factors)

- ❑ ዕድሜ መግፋት
- ❑ በዘር የጡት እንዲሁም የሌላ ካንሰር ተጠቂ ከሆነ ቤተሰብ መወለድ
- ❑ የተዛባ የአመጋገብ ዘይቤ
- ❑ የሰውነት ክብደት ከመጠን በላይ መጨመር
- ❑ የጨረር Radiation ሕክምና
- ❑ የአልከሆል መጠጦች ማዘውተር
- ❑ ሲጋራ ማጨስ
- ❑ የሰውነት እንቅስቃሴ አለማዘውተር
- ❑ ሆርሞን የመተካት ህክምና


### *የጡት ካንሰር ምልክቶች*

- ❑ ሕመም የሌለው እባጭ ወይም የጡት መጓጎል
- ❑ ጠጣር የሆነ እባጭ በብብት ስር መከሰት
- ❑ የጡት መጠን ወይም ቅርጽ መለወጥ
- ❑ ያልተለመደ ፈሳሽ በጡት ጫፍ መምጣት
- ❑ የጡት ጫፍ ወደ ውስጥ መሰርጎድ
- ❑ የጡት ቆዳ መወፈር ወይም እንደ ብርቱካን ልጣጭ ጠቃጠቆ መሰል ነገር ማውጣት

### መከላከያ መንገዶች

ምንም እንኳዋን ሙሉ በሙሉ ካንሰርን መከላከል ባይቻልም ለካንሰር ሊያጋልጡ ከሚችሉ ሁኔታዎች መጠንቀቅና የመጋለጥ አደጋን (risk) መቀነስ ይቻላል

- ❑ ቅድሚያ ምርመራን በማድረግ ወደ ሌላ ከመዛመቱ በፊት በአጭሩ መቀጨት ይቻላል
- ❑ የአኗኗር ዘዴን መቀየር
- ❑ ጤናማ አመጋገብ ዘዴን መከተል ፍራፍሬ ቅጠላ ቅጠል ማዘውተር ፣ብዙ ቅባት ያላቸውን ምግቦች አለመመገብ
- ❑ የአልከሆል መጠጦች አለመጠጣት
- ❑ ሲጋራ አለማጨስ
- ❑ የሰውነት ክብደትን መቀነስ
- ❑ እራስን በራስ መመርመር እባጭ ወይ ለውጥ አለመኖሩን ማረጋገጥ
- ❑ የ mammogram ምርመራ በወቅቱ ማድረግ




Mammogram

### የማረጋገጫ ምርመራዎች

- ❑ Mammogram (የጡት ራጅ)
- ❑ አልትራሳውንድ
- ❑ Breast MRI
- ❑ ባዮፕሲ Biopsy

### እውነታዎች

- ❑ በአሜሪካ ከ8 ሴቶች አንድዋ ለካንሰር በሽታ ይጋለጣሉ
- ❑ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሴቶች በካንሰር በሽታ ይጠቃሉ በሺዎች የሚቆጠሩት ደሞ በዚሁ በሽታ ይሞታሉ
- ❑ በ2018 በአሜሪካ (USA) 266212 አዲስ የጡት ካንሰር በሽተኞች እንደሚገኙ ተገምቷል
- ❑ የጡት ካንሰር በ3.5% እያደገ ነው
- ❑ ካንሰር ሴቶችችን በመግደል ሁለተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል


ምንጭ

https://utswmed.org/conditions-treatments/breast-cancer/



By: Mihret Woldeab RN.BSN